# አቋምህን አጠናክር፦ ድንግልና

መጽሐፍ ቅዱስ ‘ከፆታ ብልግና ራቁ’ ይላል። (1 ተሰሎንቄ 4:3) ሊያጋጥምህ የሚችለውን ሁኔታ አስቀድመህ ማሰብህ የአምላክን ሕጎች መጠበቅ የሚበጀው ለአንተው እንደሆነ እርግጠኛ እንድትሆን ይረዳሃል።




የአምላክ ሕግ
ከልክ በላይ ጥብቅ ነው?

አምላክ ያልተጋቡ ሰዎች ደስታ
የሚሰጥ ነገር እንዳያደርጉ
የሚከለክላቸው ለምንድን ነው?




የሚከተሉትን ትዕይንቶች በዓይነ ሕሊናህ ለመሳል ሞክር . . .

ትዕይንት 1

**ስሜት**

ትዕይንት 2

**ተጽዕኖ**

ትዕይንት 3

**አጋጣሚ**

ትዕይንት 4

**ውጤት**

ከጋብቻ በፊት የፆታ ግንኙነት የሚፈጽሙ አብዛኞቹ ወጣቶች በኋላ ላይ ይጸጸታሉ።
**ምክንያቱ ምን ይመስልሃል?**

______________________________

______________________________

አብዛኞቹ ሴቶች የሚፈልጉት ከጉዳት የሚጠብቃቸው እንጂ መጠቀሚያ የሚያደርጋቸው ወንድ አይደለም። ብዙዎቹ ወንዶች ደግሞ ከአንዲት ሴት የፈለጉትን ካገኙ በኋላ ያቺ ሴት ያን ያህል አትማርካቸውም።
**ምክንያቱ ምን ይመስልሃል?**

______________________________

______________________________



www.jw.org/am © 2016 Watch Tower Bible and Tract Society of Pennsylvania

# በጽሑፍ አስፍር!

ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች መልስ ስጥ።



## ትዕይንት 1 ስሜት

የፆታ ስሜት ሁልጊዜ እንደ “መጥፎ” ነገር መታየት የሌለበት ለምንድን ነው? **—ምሳሌ 5:18, 19ን አንብብ።**

---

ከፆታ ስሜት ሌላ፣ ኃይለኛ የሆነ ስሜት ሊያድርብህ አይችልም? (አንዳንዶቹን ጥቀስ።)

---

እንዲህ ያሉ ስሜቶች በውስጥህ በተቀሰቀሱ ቁጥር እርምጃ ትወስዳለህ? አዎ አይ

የፆታ ስሜትህን ልትቆጣጠረው እንደምትችል ይሰማሃል? አዎ አይ

የፆታ ፍላጎትን የፈጠረው አምላክ ራሱ፣ ራስን የመግዛት ባሕርይ እንድታዳብር ያዘዘህ መሆኑ በአንተ ላይ ስላለው እምነት ምን ያሳያል?—**1 ተሰሎንቄ 4:4ን አንብብ።**

---

## ትዕይንት 2 ተጽዕኖ

አንዳንዶች የፆታ ግንኙነት ፈጽመው በማያውቁ ወጣቶች ላይ የሚያሾፉት ለምን ይመስልሃል?

---

እኩዮችህ የፆታ ግንኙነት እንድትፈጽም የሚገፋፉህ ለምን ሊሆን ይችላል?

---

የአምላክን ሕግ እንድትጥስ ለሚገፋፉህ ሰዎች ምን አመለካከት ሊኖርህ ይገባል? **—ምሳሌ 13:20ን አንብብ።**

---





## ትዕይንት 3 አጋጣሚ

ከጋብቻ በፊት የፆታ ግንኙነት ለመፈጸም እንዳትፈተን ከየትኞቹ ሁኔታዎች፣ ሰዎች ወይም ቦታዎች መራቅ ይኖርብሃል?

---

---



www.jw.org/am © 2016 Watch Tower Bible and Tract Society of Pennsylvania

ትዕይንት 4
**ውጤት**

ለፆታ ስሜታቸው ተገዢ የሆኑ ሰዎች አብዛኛውን ጊዜ ካገቡም በኋላ ይህ አመላቸው አይለቃቸውም። ይህ እውነታ፣ ከማግባትህ በፊት የፆታ ግንኙነት ከመፈጸም የመታቀብን አስፈላጊነት የሚያሳየው እንዴት ነው?—**ገላትያ 6:7, 8ን አንብብ።**

በአንተ አመለካከት እስክታገባ ድረስ ድንግል ሆነህ መቆየት ምን ጥቅሞች አሉት?

እንደ እኩዮችህ “በነፃነት” ከመኖር ይልቅ አምላክ ከጋብቻ በፊት የፆታ ግንኙነት ከመፈጸም እንድንታቀብ የሰጠውን ትእዛዝ መጠበቅ ይበልጥ ደስተኛ እንደሚያደርግህ ይሰማሃል? እንዲህ ያልከው ለምንድን ነው?



# ዕቅድ አውጣ

**ትዕይንት 1—ስሜት**

ስሜቴ እያታለለኝ እንደሆነ ከተሰማኝ የሚከተለውን እርምጃ እወስዳለሁ፦

**ትዕይንት 2—ተጽዕኖ**

እኩዮቼ ድንግል በመሆኔ ሲያሾፉብኝ ወይም የፆታ ግንኙነት እንድፈጽም ሲገፋፉኝ እንዲህ እላቸዋለሁ፦

**ትዕይንት 3—አጋጣሚ**

የፆታ ግንኙነት ወደ መፈጸም የሚመራ ሁኔታ ካጋጠመኝ እንዲህ አደርጋለሁ፦

## ሊሳካልህ ይችላል!

አስቀድመህ አቋምህን ካጠናከርክ ተጽዕኖ በሚደረግብህ ጊዜም እንኳ ትክክለኛውን ውሳኔ ማድረግ ትችላለህ!



www.jw.org/am © 2016 Watch Tower Bible and Tract Society of Pennsylvania